8ኛ ዓመት ቁጥር 2
8th Year No. 2

ሐረር የካቲት 1996
Harar Feb. 2004

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 33/1996
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1996 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 33/1996 ........................................ ገጽ 292

## አዋጅ ቁጥር 33/ 1996 ዓ/ም
## በሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት ለ1996 በጀት ዓመት
## በሐረር ከተማ ለተከሰተው የውሀ ችግር ጊዚያዊ ማቃለያ
## የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 52 ንዑስ አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋሉ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ::

የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግሥት ም/ቤት አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀፅ 21 መሠረት የሚከተሉ የተጨማሪ የበጀት አዋጅ አውጇል::

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ በ1996 በጀት ዓመት ለመንግሥት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 33 / 1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ስለተጨማሪው የገቢ ምንጭ

በክልሉ መንግሥት ካለፉት በጀት ዓመታት ተመላሽ በጀት

3. <u>ስለ ወጭ ምደባ</u>

በሐረር ከተማ ለተከሰተው ከፍተኛ የውሃ ችግር ቦቴዎች ግዢ ለማከናወን ብር 3,000,000.00 /ሦስት ሚሊዮን ብር/ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

4. <u>ክፍያ ስለመፈፀም</u>

ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልሉ መንግሥት ውሃና ፈሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን መ/ቤት ክፍያውን ሲጠይቅ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ወጪ በማድረግ እንዲከፈል ታዟል።

5. <u>አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ <u>10/6/1996 ቀን</u> 1996 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር <u>የካቲት 10 ቀን</u> 1996

ፉአድ ኢብራሂም

ሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዝዳንት